# የኦዲት ግኝት መረጃ አመላካች

**መረጃ ሰጪው፡-** የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

**ኦዲት ተደራጊ፡-** የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

**ኦዲት የተደረገው የበጀት ዓመት፡-** የ2013 ነኛ ሩብ ዓመት

**የኦዲት አካባቢ፡-** የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት

**የኦዲት ግኝት፡-**

## 1. አዋጅንና መመሪያን ያልተከተለ የኢንሹራንስ ሽፋን ወጪ ብር 1,185,233.60

### 1.1 ሁኔታ፣

ብዛታቸው 69 ለሆኑ ለመ/ቤቱ ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎች እ.ኢ.አ ከኦገስት 7/2020 እስከ ኦገስት 6/2021 የሚውል የሞተርና የ3ኛ ወገን የኢንሹራንስ ሽፋን በብር 1,185,233.60 ከንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ ተገብቷል፡፡ ይሁን እንጂ ግዢው የተከናወነው አዋጅንና መመሪያን ተከትሎ አይደለም፡፡ ምክንያቱም፤

- ግዢው የተከናወነው ግልጽ የጨረታ ዘዴን በመጠቀም ስላልሆነ የሀብት አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ ብቃትንና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ የተፈጸመ ስለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት አልተቻለም፤
- የመ/ቤቱ የግዢ አጽዳቂ ኮሚቴ መርምሮ ግዢውን አላጸደቀውም፤
- ወጪው አምና ከተደረገው ክፍያ ጋር ሲነጻጸር የብር 223,641.25 (ብር 961,592.35-1,185,233.60) ወይም 23% ጭማሪ ያሳያል፡፡

### 1.2 መስፈርት፣

የፌደራል መንግስት የግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009፣ የፌደራል መንግስት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ፣ የፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2009፣ የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003

### 1.3 መንስኤ፣

የፌደራል መንግስቱን አዋጅና መመሪያ በተገቢው መንገድ አለመረዳት፤ አክብሮ ተግባራዊ አለማድረግ፤ ወይም ቸልተኝነትን ማሳየት፤

### 1.4 የሚያስከትለው ጉዳት፣

ግዢው የተከናወነው መንግስት ያወጣውን አዋጅና መመሪያን ያልተከተለ ስለሆነ ተጠያቂነትን ሊያስከትልና ሂሳቡም ተቀባይነትን ሊያጣ ይችላል፡፡ የኤጀንሲውንም ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

## 2. ሳይወራረዱ ከሦስት ወር በላይ የቆዩ በድምሩ ብር 48,517.40 የቅድመ-ክፍያ ሂሳቦች፤

### 2.1 ሁኔታ፣

ለተለያዩ ግዢዎች የሚውል በቅድሚያ የተከፈሉ ሂሳቦች (Prepayments) በወቅቱ መወራረዳቸውን ለማረጋገጥ ባደረግነው ማጣራት በድምሩ ብር 48,517.40 (አርባ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አስራ ሰባት ብር ከአርባ ሳንቲም) ሳይወራረዱ ከሶስት ወራት በላይ መቆየታቸው የተረጋገጠ ሲሆን ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| የሰነድ ቁጥር | የቼክ ቁጥር | ብር | የተከፈለበት ምክንያት | ገንዘቡ ከባንክ ወጪ የተደረገበት ቀን | ገንዘቡ ሣይወራረድ የቆየበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 294 | 30628483 | 35,750 | ለተለያዩ ጉዳዮች | 03/9/2020 (28/12/12) | 119 ቀናት |
| 270 | 30628479 | 9,000 | ለኮቪድ 19 አልኮል መግዣ | 24/8/2020 (18/12/12) | 129 ቀናት |
| 271 | ከፐቲ ካሽ | 920 | ለስልክ ወጪ | 20/8/2020 (14/12/12) | 133 ቀናት |
| 274 | ከፐቲ ካሽ | 2,847.40 | ለማስታወቂያ | 24/8/2020 (18/12/12) | 129 ቀናት |
| ድምር | | 48,517.40 | | | |

### 2.2 መስፈርት፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ን/አ 4ለ.

### 2.3 መንስኤ፣

በመመሪያው መሰረት በቅድሚያ የተከፈለ ክፍያ በወቅቱ እንዲወራረድ ብርቱ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረግ፤

### 2.4 የሚያስከትለው ጉዳት፣

ለመ/ቤቱ ጉዳይ ሲባል በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ ለተባለው ዓላማ በወቅቱ ስራ ላይ ላይውል ይችላል፣ ገንዘቡ ሳይወራረድ/ሳይሰበሰብ ለረዥም ጊዜ ሊቆይ ይችላል፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ ከምችት በየጊዜው እየጨመረ ሊሄድ ይችላል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agricultural Transformation Agency

# 3. ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብ ተመዝግቦ የተገኘ የቅርንጫፍ ቢሮዎች የወጪ ሂሳብ ብር 490,143.07

## 3.1 ሁኔታ፣

ደጋፊ ማስረጃ/ሰነድ ሳይኖር የሀምሌና የነሐሴ 2012 እና የመስከረም 2013 ወራት የክልል ቅርንጫፍ ቢሮዎች (አማራ፣ ትግራይ እና ደቡብ) ወጪዎች በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ተተንትነው በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ (Journal Voucher) ቁጥር 1, 2, 3 እና 8 ተመዝግበው ሪፖርት መደረጋቸው፤ ይህም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፤

| የሰነድ ቁጥር | ወር | ቅርንጫፍ ቢሮ | ጠቅላላ ብር |
|---|---|---|---|
| 1 | ሀምሌ 2012 | አማራና ትግራይ | 24,350.66 |
| 2 | ነሐሴ 2012 | አማራ | 65,306.50 |
| 3 | ነሐሴ 2012 | ደቡብና ትግራይ | 268,104.77 |
| 8 | መስከረም 2013 | ትግራይ፣ አማራ እና ደቡብ | 132,381.14 |
| **ድምር** | | | **490,143.07** |

## 3.2 መስፈርት፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9፡፡

## 3.3 መንስኤ፣

ከመ/ቤቱ የክልል ቅርንጫፍ ቢሮዎች በየወሩ መጨረሻ ሰነዶች ዋና መ/ቤት እንዲመጡ ተገቢውን ክትትልና ጥረት አለማድረግ፤

## 3.4 የሚያስከትለው ጉዳት፣

ወጪው ተቀባይነትን ላያገኝና መመሪያን የተከተለ አመዘጋገብ ስላልሆነ ሂሳቡ ተቀባይነትን ሊያጣና ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡ያለማስረጃ ተከፍሎም ከሆነ የመንግሥትን ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

# 4. ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት በወቅቱ አለመቅረብ፤

## 4.1 ሁኔታ፣

ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት ተከታዩ ወር በገባ በ15 ቀናት ውስጥ በአድራሻ ለገ/ሚር እና በቅጂ ለመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት የስራ ክፍል ባለመቅረቡ ምክንያት በአማካይ ከ77 ቀናት በላይ መዘግየቱ፣

## 4.2 መስፈርት፣

የፋይናንስ ኃላፊነትን በአግባቡ ባለመወጣት የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች መመሪያ ቁጥር 48/2009 አንቀጽ 10.1.1

## 4.3 መንስኤ፣

መመሪያው ላይ በተቀመጠው መሰረት ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት በወቅቱ ለማቅረብ ተገቢውን ጥረት አለማድረግ፤ በኮምፒውተር የትግበራ ስርዓት ላይ በቂ ልምድ አለመኖር፤የሰው ሃይል እጥረት፤

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agricultural Transformation Agency